DISCOVER
ITS BEAUTY

ክፍል 5

# አላህ

(ብቸኛው እውነተኛ አምላክ)

# የእርሱ መልካም ስሞች

ዶ/ር ናጂ ኢብራሂም

بسم الله الرحمن الرحيم

# በአላህ ስም

## እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በኾነው እጀምራለሁ።

# አላህ (ብቸኛው እውነተኛው አምላክ)
# የእርሱ መልካም ስሞች

የተከበረው ቁርኣን እና ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ስለ ብቸኛው እውነተኛ አምላክ የአላህ ስሞች ያስተምሩናል። ለምሳሌ ቁርኣን እንዲህ ይላል፡-

- **ለአላህም መልካም ስሞች አሉት፡፡ (ዱዓ ስታደርጉ) በእርሷም ጥሩት፡፡** (7:180)

አላህን ስንማፀን በመልካም ስሞቹ ወይም ከጥያቄያችን ወይም ከፍላጎታችን ጋር በሚገናኘው ስሙ እንድንጠራው እንበረታታለን። ለምሳሌ፣ ጥያቄያችን የሕይወታችንን አቅርቦት የሚመለከት ከሆነ፣ አል-ረዛቅ፣ ሰጪው ብለን ልንጠራው እንችላለን። እነዚህ ስሞች አላህ ከአንድ በላይ መሆኑን አያመለክቱም፤ የአላህ ብቸኛው አምላክ የሆኑትን ልዩ ልዩ ባህሪያትን የሚገልጹ ስሞች ናቸው።

እኛ የሰው ልጆች የአላህን ታላቅነት በፍፁም በአእምሯችን ልንገነዘበው አንችልም ነገርግን ስለእርሱ እና እርሱን የሚያስደስተውን ባወቅን መጠን እርሱን መውደድ እና ማምለክ እንችላለን። ስለ አላህ መማር - ስሞቹን እና ባህሪያቱን በማጥናት እና በመረዳት - በዚህ ህይወትም ሆነ በሚቀጥለው ህይወት የአእምሮ ሰላም ያስገኝልናል ምክንያቱም ሁሉም ነገር በእጁ እንዳለ እና እንደ ፈቃዱ እንደሚፈጸም ስለምንቀበል ነው።

ለፍጡራን ለአላህ ብቻ የተገባ የሆነን ስም መጠቀም ተገቢ አይደለም። ብዙውን ጊዜ ሙስሊሞች በ "አብዱል" የሚጀምሩ ስሞች አሏቸው (ማለትም "የ....አገልጋይ" ማለት ነው) ቀጥሎም ከአላህ ስሞች አንዱን በማስከተል ነው። ስለዚህም አብዱላህ ማለት የአላህ ባሪያ (አገልጋይ) ማለት ነው፡ አብዱረህማን ማለት ደግሞ "የአልራህማን" (አዛኙ) አገልጋይ ወዘተ ማለት ነው።

# አር-ራሂም




በጣም ሩህሩህ የሆነው። (በሱ ልክ ለሰዎች እዝነት ሊኖረን ባይችልም፣ ልናደንቀው እና ለሌሎች መሐሪ ለመሆን የተቻለንን ሁሉ መሞከር እን ችላለን።)

ስለ እውነተኛው አምላካችን የአላህን ስሞች የበለጠ ማወቅ እና በሱ እና በባህሪያቱ ማመን፣ አንዳችንን ነገር በምናደርግበት ጊዜ ወይም ከሌሎች ጋር በተገናኘን ጊዜ አላህ፡- እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ፣ እጅግ በጣም መሐሪ፣ ዳኛ፣ ሁሉን አዋቂ፣ ሁሉን ተመልካች፣ ይቅር ባይ፣ እጅግ በጣም ቸር፣ እውነት፣ ወዘተ መሆኑን እንድናስታውስ ያደርገናል።

እነዚህን መልካም ባህሪያት አቅማችን በፈቀደው መጠን በራሳችን ህይወት ውስጥ ተግባራዊ ማድረጋችን አስፈላጊ ነው።



አሁን ስለ አላህ ስሞች የበለጠ እንማር



# አስ-ሳላም

السَّلَامُ

ከጉድለት የፀዳ የሰላም እና የፍጽምና ምንጭ። እሱ ሁልጊዜ ፍጹም ነው፤ እንደ መታመም፣ መራብ፣ መጠማት፣ በብርድ መጠቃት ያሉ የሰው ባህሪያት የሉትም።

**በአረብኛ ካሉት መልካም የአላህ ስሞች ጥቂቶቹ እና በአማርኛ ትርጉሞቻቸው፦**

**አላህ፦** የእውነተኛው ብቸኛው አምላክ ስም።

**አር-ራህማን፦** ለፍጡራን ሁሉ በጣም አዛኝ እና እጅግ በጣም ሩህሩህ የሆነው።

**አር-ራሂም፦** በጣም ሩህሩህ የሆነው። (በሱ ልክ ለሰዎች እዝነት ሊኖረን ባይችልም፣ ልናደንቀው እና ለሌሎች መሐሪ ለመሆን የተቻለንን ሁሉ መሞከር እንችላለን።)

**አል-ማሊክ፦** በሰማያትና በምድር ሁሉ ላይ ሥልጣን ያለው ሉዓላዊ ጌታ።

**አን-ኑር፦ ቀጥተኛ መንገድን የሚመራ፣ (የሚያበራን እና የሚመራን።) አል-ኑር በተሰኘው ምእራፍ ቁርኣን "አላህ የሰማያትና የምድር ብርሃን (አብሪ) ነው" ይለናል።** (ቁርኣን 24፡35)

**አል-ቁዱስ፦** ቅዱስ፣ ንጹሕ፣ የተባረከ (አጋር ከመኖር፣ ከልጅ፣ ከፍጡራን ባህሪ የጠራ)።

**አስ-ሳላም፦** ከጉድለት የፀዳ የሰላም እና የፍጽምና ምንጭ። እሱ ሁልጊዜ ፍጹም ነው፤ እንደ መታመም፣ መራብ፣ መጠማት፣ በብርድ መጠቃት ያሉ የሰው ባህሪያት የሉትም።



# አር-ራዛቅ




ሁሉን ሰጪ፣ ለሁሉም ህይወት ያለው ነገር ሲሳይን፣ ደህንነትን እና መመሪያን የሚሰጥ ነው። እያንዳንዳችን የተጻፈልንን ድንጋጌ እንቀበላለን ነገር ግን - በማጭበርበር ወይም በሙስና ሳይኖን በተፈቀዱ መንገዶች ብቻ ልን ሰራበት ይገባል።

# የእርሱ መልካም ስሞች የቀጠለ....

**አል-ባሲር፡-** ሁሉን ተመልካች፣ በአጽናፈ ሰማይ ውስጥ የሚከናወነውን ሁሉ የሚያይ።

**አስ-ሳሚዕ፡-** ሁሉን ሰሚ፣ ሁሉንም ነገር የሚሰማ፤ ስንጠራው ወይም ስንጸልይ (ዱዓ ስናደርግ) እርሱ ይሰማናል።

**አል-አዚም፡-** ታላቁ፣ በፍጥረቱ ውስጥ ከማንኛውም ነገር ወይም ከማንም በላይ ታላቅ የሆነ።

**አል-ጋፉር፡-** ሁሉን መሓሪ፣ የተጸጸቱትን እና ወደ እርሱ የተመለሱትን ያለማ ቋረጥ ይቅር የሚል።

**አት-ተውዋብ፡-** ንስሐን (ተውባ) የሚቀበል። አላህ ኃጢአተኞች ወደ እርሱ እንዲጸጸቱ ይወዳል እና የኛን እውነተኛ ንስሐ ያለማቋረጥ ይቀበላል። በአንጻሩ የሰው ልጅ፣ ለእኛ ቅርብ የሆኑትም ቢሆን፣ ውሎ አድሮ ስህተቶቻችንን ለመቀ በል እና ከዛ በኋላ በተመሳሳይ ስሜት አኛን መቀበል ያደክማቸዋል።

**አል-ዐሊይ፡-** ከፍ ያለ፣ የላቀ፣ ከፍጡራን ሁሉ በላይ የሆነ።

**አል-ዋዱድ፡-** ጻድቃን እና ታዛዥ የሆኑትን የሚወድ፣ እና ያንን ውዴታ በእለት ተዕለት ህይወታችን ውስጥ የሚገልጥልን። ለውዴታው አድናቆት ማሳየት አለብን፣ እናም ለራሳችን የምንመኘውን ለሰዎች በመመኘት ሌሎችን መውደድ አለብን።



# አል-ዋዱድ




ጻድቃን እና ታዛዥ የሆኑትን የሚወድ፣ እና ያንን ውዴታ በእለት ተዕለት ህይወታችን ውስጥ የሚገልጥልን። ለውዴታው አድናቆት ማሳየት አለብን፣ እናም ለራሳችን የምንመኘውን ለሰዎች በመመኘት ሌሎችን መውደድ አለብን።

**አል-ሀከም፦** ዳኛ፣ ፍርዱ ፍጹም ትክክለኛ እና ፍትሀዊ የሆነ (ከሱ ማምለጥ የማይቻል ነው)።

**አል-ዐሊም፦** ሁሉን አዋቂ፣ ያለፈውን፣ የአሁኑን እና የወደፊቱን ጨምሮ የሚ ታየውን እና የተደበቀውን ሁሉ የሚያውቅ። **ከቅጠልም አንዲትም አትረግ ፍም የሚያውቃት ቢኾን እንጅ።** (ቁርኣን 6፡59)

**አር-ሩኡፍ፦** በጣም ቸር፣ ርህራሄው፣ ገርነቱ፣ እዝነቱ እና ምህረቱ ገደብ የለሽ የሆነው።

**አር-ራዛቅ፦** ሁሉን ሰጪ፣ ለሁሉም ህይወት ያለው ነገር ሲሳይን፣ ደህንነትን እና መመሪያን የሚሰጥ ነው። እያንዳንዳችን የተጻፈልንን ድንጋጌ እንቀበላለን ነገር ግን - በማጭበርበር ወይም በሙስና ሳይኖን በተፈቀዱ መንገዶች ብቻ ልንሰራበት ይገባል።

**አል-ሀቅ፦** እውነትኛ፣ ቃሉ እውነት የሆነው ብቸኛው እውነተኛ አምላክ። እርሱ የውሸት ተቃዋሚ መሆኑን አውቀን እዉነታው እኛን የሚደግፍ ቢሆንም ባይ ሆንም በምንናገረው እና በምናደርገው ነገር ሁሉ እውነትን ለማግኘት እና ለመያዝ መጣር አለብን።

**አል-ሀሊም፦** ትዕግሥተኛ፣ የተረጋጋ፣ ታጋሽ፣ ከኃጢአተኞችም፣ ከበደለኞ ችም፣ ከእነዚያም ከካዱት ወይም በሱ ከማያምኑት ጋር እንኳ የማይቸኩል ነው። አላህ ስህተቶቻችንን ቸል ይላል እና በዙሪያችን ላሉት ሰዎች ተመሳሳይ ነገር ለማድረግ መጣር አለብን ምክንያቱም እንዚያ ቂም የሚይዙት እራሳቸ ውን ቢሆን እንጂ ማንንም አይጎዱም።



# አል-ሙጂብ

ምላሽ የሚሰጥ፣ ጸሎታችንን የሚቀበል። አላህ እርዳታውን በዱዓ እንድንለምን ይወዳልና ዱዓ ችንንም መቀበልን ይወዳል።

# የአላህ ባህሪያት እና ደረጃዎች

ብቸኛው እውነተኛውን አምላክ (አላህ) ከሌሎች አምላክ ነን ከሚሉት ከሚለ ዩት ባህሪያት እና ደረጃዎች በጥቂቱ፦

- ብቸናው እውነተኛው አምላክ (አላህ) በባህሪያቱ ልዩ ነው። እርሱን የሚመስ ለው ማንም የለም፣ የሰውም ሆነ የእንስሳት ባህሪያት ለእርሱ ሊሆኑ አይች ሉም።
- ይህ እውነተኛ አምላክ ፈጣሪ ነው፤ አልተፈጠረም አልተወለደም።
- ብቸኛው እውነተኛ አላህ (አምላክ) እርሱን ብቻ እንድናመልከው አድርጎ ፈጥሮ ናል። አላህን ብቻ ስናመልክ ከጣዖት አምልኮ፣ ከቅዱሳን፣ ከታዋቂ ሰዎች፣ ከገን ዘብ ወይም ከማንኛውም ነገር አምልኮ ነፃ እንወጣለን።
- እውነተኛው አላህ (አምላክ) አንድ እንጂ ሦስት ወይም ከዚያ በላይ አይደለም! አጋሮችም ሆነ አቻዎች የሉትም።
- አላህ (አምላክ) በዚህ ህይወት (በዱንያ) በሰውም ሆነ በሌሎች ፍጥረታት አይ ታይም (በምንም የፍጡር አምሳያ አይገለጽም)።
- አላህ (አምላክ) ለፍጡራኑ በምንም መልኩ በአካል አልተገለጠም።
- አላህ (አምላክ) ዘላለማዊ ነው፤ አይሞትም አይለወጥም።
- አላህ (አምላክ) ምንም ወይም እንደ እናት፣ ሚስት ወይም ልጅ አይፈልግም፤ ወይም ምግብ፣ መጠጥ፣ ወይም ምንም ዓይነት እርዳታ አይፈልግም። እሱን የሚፈልጉት ሌሎች ናቸው።

እነዚህን መመዘኛዎች እና ባህሪያት (እንዲሁም ሌሎች የእርሱ ብቻ የሆኑትን) ተጠቅመን አንድን ሰው ወይም አንድን ነገር አላህ (አምላክ) ነው የሚለውን ማንኛውንም ጥያቄ መገምገም እንችላለን።

# የማወቅ ጉጉት አልዎት?

የማወቅ ጉጉት ካሎት እና ስለ እስልምና ተጨማሪ መረጃ እና ዝርዝር መረጃ ለማግኘት ከፈለጉ እባክዎን ድረ-ገጻችንን ይጎብኙ፡-

**www.discoveritsbeauty.com**

## የውበቱን ያግኙ ተከታታይ ቡክሌቶች፡-

1. **ከብዙው በትንሹ**
2. **የአደም እና የሐዋ ሃይማኖት**
3. **የእስልምና መሠረቶች**
4. **የሰብአዊነት ወሳኝ ጥያቄዎችን መመለስ**
5. **የእርሱ መልካም ስሞች**
6. **የመጨረሻው ወህይ**
7. **የመጨረሻው መልእክተኛ**

## ጠቃሚ ኢስላማዊ ድረ-ገጾች፡-

**http://www.allahsquran.com**

**http://www.quranexplorer.com**

**http://www.islamhouse.com**

**http://www.edialogue.org**

**http://www.islamreligion.com**

**http://www.newmuslimguide.com**

**http://www.guidetoislam.com/en/**

# የእምነት ምስክርነት (የእስልምና መግቢያ በር)

“ከአላህ በስተቀር በእውነት እና በብቸኝነት የሚመለክ ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ ሙሐመድም የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን እመሰክራለሁ።”


በአረብኛ እንዲህ ይነበባል፡-

أشهد أن لا إله إلا الله وأشهد أن محمدا رسول الله

ሲነበብ ይህን ይመስላል፡-

**አሽ-ሀዱ አላ ኢላሀ ኢለ ሏህ**
**ወ አሽ-ሀዱ አነ ሙሐመደን ረሱሉሏህ**

ይህ አንድ ሰው እስልምናን ለመቀበል በአፉ መናገር ያለበት የእምነት ምስክርነት ነው። የእስልምናን እውነተኛነት፣ ውበት እና ቀላልነት አንድ ላይ ይዟል።






DISCOVER
ITS BEAUTY
www.discoveritsbeauty.com

ይቃኙት

GLOBAL ACADEMY FOR TRANSLATION AND EDUCATION (GATE)
LONDON | THE UNITED KINGDOM

በAL-ANDALUS GROUP LTD የተተረጎመ
www.alandalusgroup.org

كتاب أسماء الله الحسنى باللغة الأمهرية